# <u>ትምህርተ - ዜግነት</u>

## *<u>ሀገር ማለት ምን ማለት ነው?</u>*

## *<u>ክፍል አንድ</u>*

*ከሥርጉተ ሥላሴ*
*ሐምሌ 2000 ዓ.ም.*

እንደምን አላችሁ? ደህና ናችሁ?
ልጆች !
ልጆች ሀገር ማለት ምን ማለት ነው? ሀገር ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ባለው የወሰን ክልል የሚገኝ መሬት ማለት ነው።
ልጆች አሁን ኢትዮጵያ ዓለም ዓቀፍ ዕውቅና ባለው የወሰን ክልል የሚገኝ መሬት ስላላት ኢትዮጵያ ሀገር መሆን ችላለች።
ሀገር - አለን ልጆች
መፈጠሪያ - አለን ልጆች
መጠጊያ አለን ልጆች
መኩሪያ አለን ልጆች
መመኪያ - አለን ልጆች ማን ? ኢ ት ዮ ጵ ያ
አዎ ልጆች ኢትዮጵያ ሀገራችን
የጀግኖች እንምባ
የጨዋ ሕዝብ ማማ።
የሰው ልጆች ሁሉ መፈጠሪያ ማዕከል ናት ማን? ኢ ት ዮ ጵ ያ
አዎን ልጆች በድንበሯ ዙሪያ ያለው የወሰን ክልል በሙሉ ያለው መሬት የማን መሬት ይባላል? <u>የኢትዮጵያ መሬት ይባላል</u>። <u>የሀገራችን መሬት ይባላል</u>።
ልጆች፡- የዜግነት ደሙ ደግሞ የሀገሪቱ መሬት ወይንም አፈር ነው። የሰው ልጅ ሲፈጠር መሠረቱ ከአፈር ነው። ልጆች፡- አንድ ነገር ለመሆኑ …“ <u>ዕትብት</u> “ ማለት ታውቃላችሁ? … “ዕትብት“ ማለት ልጆች በእናታቸው ማህፀን ለ 9 ወራት ወይንም ለ 9 ወራት ከአምስት ቀን ሲቆዩ… እናትና ልጁን የሚያገናኝ ልዩ የፍቅር ድልድይ ነው። ልጅ ሲወለድ ከእናንቱ ማህፀን ስለሚወጣ ዕትብቱ ይቆረጣል።
ታዲያ ፡- የተቆረጠው ዕትብት የእንግዲህ ልጅ ከሚባል ጋር መሬት ውስጥ ይቀበራል።
አሁን የኔ ወርቆች ወደ ተነሳሁበት… የአንድ ሀገር ልጅነት የሚገኘው ዕትብቱ ከዚያ ከመሬቱ የተቀበረ ወይንም የወላጆቹ ዕትብት ወይንም የአያቶቹ ዕትብት ከዚያ የተቀበረ የዚያች ሀገርን ልጅነት ያገኛል።ይህ ማለት የህፃኑ ደም ከሀገሪቱ ደም ከሆነው ከአፈሩ ጋር በመዋሀዱ የዚያችን ሀገር ልጅነት ያገኛል። ይህ በፍፁም ሁኔታ ከምንም ነገር በላይ በእግዚአብሔር አምላካችን ጥበብ የእናትና የልጅን ፍቅር በፍፁም ሁኔታ የሚያገናፅፍ ልዩ ሂደት ነው።
ወላጆች አባካችሁን የኢትዮጵያን ሙሉ የወሰን ክልሏን የሚያሳየውን ካርታዋን ለልጆቻችሁ እንድታሳዩልን።
ለትብብራችሁ በጣም እናመሰግናለን!
ክፍል ሁለት ይቀጥላል…